(እንጦንዮስ) አምርሮ አለቀሰ። ጳውሎስ ግን፣ «የራስህን ጥቅም ብቻ መመልከት የለብህም። ሌሎች መኮሳት ካንተ አኗኗር ምሳሌ ማግኘት ይገባቸዋል። ይልቅስ አቡኑ አትናቲዎስ የሰጠህን ካባ አምጣልኝ» አለው። ስለ ካባው ጉዳይ አንቶንዮ በመስማቱ ተደነቀ። ወደ መጣበትም በመመለስ ካባውን ይዞ ሲጓዝ፣ «ጳውሎስ በዕልፍ አእላፍ መላእክት ታጅዐ ወደ ሰማይ ሲወጣ አየ። ወደ ዋሻው ገብቶ ሲመለከት ግን፣ ጳውሎስ እጁን ወደ ላይ እንደ ዘረጋ ተንበርክኮ ሞቶ አገኘው።» በዚህ ወቅት ስለ ቀብሩ እያሰበ ሳለ ሁለት አንበሶች ገስግሰው ደርሰው የመቃብሩን ስፍራ ቆፍረው አስተካክለው ተመለሱ። አንቶንዮም «ውድ የሆነውን ሽክም በደካማ ትከሻው ተሸክሞ በጉድጓዱ ውስጥ ቀበረው፤ በማግስቱም ወደ መጣበት ተመልሶ ታሪኩን ሁሉ ለደቀ መዛሙርቱ መሰከረ፤ በፋሲካና በበዓለ ኀምሳ ዕለት ያንን የጳውሎስን ካባ በመልበስ በ105 ዓመቱ በ356 ዓ.ም. አረፈ» ይላል። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ፣ በሳሙኤል ዝዋርትሁድ፣ 1988፣ ገጽ 64-68)።

# ምዕራፍ አሥራ አራት

## መሐመድ - ማንነቱ እና እምነቱ

## ክፍል አንድ

ከአይሁድ እምነት በፊት የነበሩት ሃይማኖቶች መሥራቾቻቸው ልዑላን ነበሩ፤ ቡድሀ፣ ኮንፊሺየስ፣ ዞረአስተር እና መሰሎቻቸው ልዑላን ነበሩ። ከጥሪው በኋላ ተንከራታች ቢሆንም፣ አብርሃምም ቢሆን በሀብቱ የተከበረ የባቢሎን ታዋቂ ሰው ነበር። ከጥሪው በኋላ ወደ እረኝነቱ ቢያዘግምም፣ ሙሴም በንጉሥታት ቤተሰብ ውስጥ ነበር ያደገው።

በተያያዥ፣ ኢየሱስ ከደሀ ቤተሰብ የሆነ ጠራቢ ሲሆን፣ መሐመድ ደግሞ ግመል ነጂ ነበር። ይህ የግመሎች ወዳጅ «ተገለጠልኝ» ካለው እምነት ተነሥቶ ሥራውን በጀመረ በመቶኛው ዓመቱ የጥንቱን ዓለም እኩሌታ ተቆጣጠረው፤ በተለይ ክርስትና ያልደረሰበትን ሙሉ



በሙሉ፣ ደርሶም የተንገዳገደበትን ስፍራዎች ሁሉ በማሸነፍ የእምነቱ ምርኮኛ አደረጋቸው።

* * *

የዐረቢያ ሰላጤ በዓለም ካሉት በረሀዎች በስፋቱ ተጠሪ ሆኖ ዋነኛ አገራትን ያገናኛል፣ ያካካል፣ እስራኤልን፣ ግብፅን፣ ሶሪያን፣ ቱርክን፣ የቀይ ባሕር ዳርቻን፣ እና የፋርስ (Persian) ባሕረ ሰላጤን ይነካካል።

በዐረቢያ ሁለት ስሙ-ጥር ጐሳዎች አሉ – ቤድዊን (Bedouin) እና ኩዋሪሽ (Quwarish)። እነዚህ ሕዝቦች በጥንቱ ዓለም የሰውን ልጅ እንደ ዕቃ በመነገድ ታዋቂ ነበሩ። ለዐረቦቹ የሴቶች ድርሻ ብዙ ልጆችን መውለድ ነው። ሕፃናቱ ተወልደው ማደግ እንደ ጀመሩ ወደ ሱሜሪያ (Sumerian)፣ አካዲያን (Akkadian)፣ ባቢሎን እና ወደ ሌሎች ከተሞች ይጓጓዛሉ፤

* * *

የዐረቦች እምነት ከተፈጥሮ ጋር ተያያዥ ነው፤ ሰማያት፣ ከዋክብት፣ ዛፎች፣ የገዘፉ ዐለቶች የመለኮታዊ ማንነት ሽርፍራፊ በእነርሱ ዘንድ እንዳለ ያምናሉ፤ እነዚህን ሁሉ ደግሞ አያይዞ አቀራርቦ የሚያማክላቸው በመካ የሚገኘው ካባው (ጥቁር ዐለት) ነው።

* * *

የቤድዊን ዐረቦች መኖሪያቸው በረሀው ነው፤ የኩዋሪሾቹ ደግሞ የዐረቢያ የባሕር ዳርቻዎች ናቸው። እነርሱ ከሌላው ዓለም ጋር በመገናኘት ንግድን ለምደዋል። ቤድዊኖች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ወደ እነርሱ በመሄድ ወይም በመምጣት ይገበያያሉ፤ ይህ ሒደት እስከ አንደኛው ክፍለ ዘመን እኩሌታ ቀጥሎ፣ ከ70 ዓ.ም. በኋላ ግን በመካከላቸው ሌሎች ሕዝቦች ገቡ- ዕብራውያን (አይሁዶች)። የዕብራውያኑ የመጉረፋቸው ምክንያት ሁለት ነው። አንደኛው፣ ለሮም አንገብርም ያሉ የአይሁድ ቀናተኞች (መቃባውያን) ባደረጉት ጦርነት ኃያሉ የሮም መንግሥት አይሁዶችን አስገበረ፤ ቤተ መቅደሳቸውንም አወደመ።

ፀሐይንና ጨረቃን ከሥልጣኑ በታች አደረጋቸው:: እስቲ የተፈጠሩትን ሁሉ ተመልከቱ . . . ወዮ እናንተ እምነት የሌላችሁ፣ እኔ ግን የምትስግዱለትን ጣዖት የማመልክ አይደለሁም፣» በማለት ፍጥረቱ በራሱ ተአምራቱ መሆኑን በመግለጽ ሌላ ተአምርን አትፈልጉ ይል እንደ ነበር ተጽፎለታል::

የዓለም ታሪክ አይሁዶች መዲናን እንደ መሠረቱ ይገልጻል፤ የእስልምና ገለጻ ደግሞ መሐመድን የመካ ሰዎች በተቃወሙት ጊዜ ሸሽቶ የሄደው ያትሪብ ወደምትባል መንደር ነበር:: ለኑሮና ለትምህርት ስለ ተመቸው ስሟን በመቀየር መዲና ተባለች፣ ትርጓሜውም «የነቢዩ መዲና» ማለት ነው ይላል::

## ብቸኛው በተአምራት የገነነ ነቢይ-መሐመድ

## መሐመድ ሲወለድ ምን ሆነ?

መሐመድ በተወለደ ጊዜ «በዓለም ውስጥ ያሉ ጣዖቶች ሁሉ ተንቀጥቅጠው ከቆሙበት ስፍራ ላይ እየተፈነቀሉ ወደቁ . . .» መሐመድ መጀመሪያ ዐይኑን ሲገልጥ ጣዖቶቹን ወደ ሰማይ እንሥቶ «ላ! ኢላሃ አላህ መሐመድ ረሱል አላህ (ሌላ አምላክ ያለ አላህ የለም፣ መሐመድም የአላህ ነቢይ ነው)» አላቸው::

### አፋዊ ታሪክ 1

የፋርስ ንጉሥና ሚኒስትሮቹ ከዕለታት አንድ ቀን ሌሊት ወጥተው በከዋክብት ብርሃን የደመቀውን ሰማይ ሲመለከቱ በድንገት የአንድ ኮከብ ብርሃን ከዐሐይ ይበልጥ አንጸባርቆ አዩት . . . እነርሱም፣ «ዛሬ ትልቅ ነቢይ ተወልዷል» ማለት ነው ብለው አመኑ:: በዚያን ሰዓት የመሐመድ እናት በምጥ ላይ ነበረች::

### አፋዊ ታሪክ 2

መሐመድ በተወለደ ጊዜ ተራራዎች ደነሱ፣ ዘፈኑ፣ ዛፎችም በደስታ በሹክሹክታ ተነጋገሩ፣ «ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድ ነቢይ ነው» ተባባሉ፣ አዕዋፍ ዘመሩ፤ በባሕር ውስጥ ያሉ ፍጥረታት ከውኃ ብቅ እያሉ እነሆ፣ ጊዜው መጣ፤ አሁን ዓለም የሚመራው ብርሀን አለው» አሉ::



### አፋዊ ታሪክ 3

ታሙስ የተባለው ታላቅ ዓሣ 700,000 ጅራት አለው:: ጀርባው ስፊ ከመሆኑ የተነሣ 700,000 ሠንጋ በሬዎች በጀርባው ላይ ሲፈነድቁ ምንም አይመስለውም፤ መሐመድ በተወለደ ጊዜ «ታሙስ ደስ ብሎት በጅራቱ ተንቀሳቀሰ፣ በዚህ ሰዓት መሬት ተንቀጠቀጠች:: አላህ በቶሎ ታሙስን ፀጥ ባያደርገው ኖሮ መሬት ተገለባብጣ ሁሉም ያከትምለት ነበር::»

### አፋዊ ታሪክ 4

መሐመድ እራስ ላስ ብዙ ሰዎች ሲያዩት ይመጡ ነበር፣ ከዐይኑ ታላቅ ብርሀን ይወጣ ነበር፣ ጠያቂዎቹም ዐይናቸውን ይጋርዱ ነበር::

### አፋዊ ታሪክ 5

ሰባት ሺህ መላእክት በሰማይ ጠል የተሞላ አንድ የወርቅ ሳህን አምጥተው ገላውን በዚያ ይታጠብ ነበር:: ከዚህም የተነሣ፣ ከመኝታው በተነሣ ቁጥር ንጹሕ ነበር::

### አፋዊ ታሪክ 6

መሐመድ የግመል እረኛ በነበረ ጊዜ ትኩሳት አይሰማውም፣ ምክንያቱም ትንሽ ደመና ሁልጊዜ በየሄደበት ከእናቱ ላይ ሆና ትከተለው ነበርና ነው::

### አፋዊ ታሪክ 7

ሌሊት ሌሊት የመሐመድ ዐይኖች እንደ ፀሐይ ያበሩ ስለ ነበረ፣ በጨለማ የወደቀ ደቃቅ ነገርን እንኳ ያለ ችግር ያነሣ ነበር::

### አፋዊ ታሪክ 8

መሐመድ በበረሃ ላለ ልብሱን ማውለቅ ፈልጎ ሰዎችን አፈረ፤ በግራ እና በቀኝ በሩቅ ያሉትን ዛፎች በጠራቸው ጊዜ መጥተው ጋረዱት፣ ያለ ችግርም ልብሱን ቀየረ::

### አፋዊ ታሪክ 9

መሐመድ መካን ድል ባደረገ ጊዜ ንስር በቀስቱ ላይ ያስበት በትር ተሸለመ፤ እርሱ ግን የጣዖትን ምስል ይቃወም ስለ ነበረ፣

የንስር ምልክት ያለበትን ስጦታ ቤቱ ይዞ መግባት አልፈለገም፤ እጁንም በቀስቱ ላይ ሲያደርግ ንስሩ ሕይወት አግኝቶ ስለ በረረ፣ ቀስቱን በነጻነት መያዝ ቻለ።

## አፋዊ ታሪክ 10

በሞቱም ጊዜ በአልጋው ሥር መቃብሩ ተቆፈረ፤ በቁፋሮውም ወቅት ከሩቅ የሚያበራ ድንጋይ አገኙ፣ ይህንንም አውጥተው በነቢዩ መሐመድ መቃብር ላይ አኖሩለት።

* * *

እነዚህን የመሰሉ ሌሎች በርካታ አፋዊ ታሪኮች እንዳሉ ልብ ማለት ተገቢ ነው። ለምን ይሆን ከማንም ነቢይ በላይ ለመሐመድ አፈ ታሪክ የበዛለት? የክርስትና መሠረት እና እውነት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የመሰሉ አፋዊ ታሪኮች የሉትም፤ አርግጥ ገዳማዊነት እየተስፋፋ በነበሩባቸው ዘመኖች «ክርስቲያናዊ» አፈ ታሪኮች በየመልኩ ተፈብርከዋል። እነዚህ ግን በሐሰት እውነትን ለማሳደግ የተደረጉ አጉንሎች ነበሩ። (ኃይሉ ገብርኤል ነገሮ፣ *ታላላቅ ሃይማኖቶች እንዴት ተጀመሩ?* 1955፣ ገጽ 275-306።)

***መሠረታዊ ቁም ነገሮች፡-*** እስልምና ሊታመን በማይችሉ የነቢዩ ገድሎች መሞላቱ ብቻ ሳይሆን ጥያቄን የሚፈጥረው፣ በአስተምህሮ ደረጃ የቀመራቸው ትምህርቶቹ ክርስቶስን ያማከሉ እንደ ነበሩ ተከታዮቹን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎችን ልብ በሉ።

***



| | |
|---|---|
| የኢየሩሳሌም ጉባኤ መነሻ፡- ደኅንነት በጸጋ እና ሕግም ነው አለ → | 51 ዓ.ም. ደኅንነት በጸጋ ብቻ |
| የኒቂያ ጉባኤ አርዮስ-ኢየሱስ ፍጡር ነው አለ። → | 325 ዓ.ም. ኢየሱስ አምላክ ነው! |
| የቁስጥንጥንያ ጉባኤ-አቡሊናርዮስ በሥላሴ መካከል መበላለጥ አለ፤ መቅደንዩስ መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ውስጥ የተሰራጨ ፍጡር ነው አለ። → | 381 ዓ.ም. እኩልነት- በሥላሴ ሁሉ- መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው! |
| የኤፌሶን ጉባኤ 1ኛ ፔላጂየስ የአዳም ኃጢአት ለልጆቹ አይተላለፍም አለ። ንስጥሮስ ኢየሱስ ከድንግል አልተ ወለደም በሕፃንነቱም ሊሰገድለት አይገባም አለ። → | 431 ዓ.ም ሰዎች ሁሉ ከአዳም የተነሣ በኃጢአት ተወልደዋል። |
| የኤፌሶን ጉባኤ 2ኛው አውጣኪ ፍጹም ሰውነቱ በመለኮቱ ውስጥ ተውጦ ቀርቷል አለ። → | 449 ዓ.ም በመለኮት ላይ ሰውነት ተደረበ እንጂ፣ ኢየሱስ ከማርያም ቢወለድም ሊሰገድለት የተገባ ነው። |
| የቀልኬዶን ጉባኤ፡- የኢየሱስ ሁለት ባሕርይ የመቀላቀል ጠባይ አለው። → | 481 ዓ.ም የኢየሱስ ሁለት ባሕርይ ያለመቀላቀል አብረው አሉ፣ ይኖራሉ። ይላል። |

እስልምና በ570 በተወለደው መሐመድ ሲጀምር፣ ክርስቲያኖች 51-481 ያካሄዷቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሌላኛውን ሃይማኖት መፍጠሩን የታሪክ ተመራማሪዎች ይስማሙብታል። ነቢዩ መሐመድ ተቀባይነቱን ያሰፋ ዘንድ የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን በማጣጣም ለእርሱ እንቅስቃሴ ዋንኛ መንደርደሪያ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ፣ ነቢዩ በ40 ዓመት ወደ ዋሻው ደርሶ በ40 ቀን ቆይታው ገብርኤል የገለጠለትን ሲያስተምር፣ የ40 ቁጥር መለኮታዊ ገጽታን ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አኳያ አብራርቷል።

- በኖኅ ዘመን ለ40 ቀናት ዝናብ ዘንቧል።

- ሙሴ የተጠራው በ40 ዓመቱ ሲሆን፣ በሲና ተራራ የቆየው ለ40 ቀናት ነበር።
- ሰላዮች የተሰፋዪቱን ምድር የሰለሉት ለ40 ቀናት ነበር።
- በዳዊት ዘመን የጎልያድ ተግዳሮት ለ40 ቀናት ነበር።
- ሰነነዌ የንስሐ ወቅት 40 ቀናት ተቈረጠ።
- ኢየሱስ ለ40 ቀናት በምድረ በዳ ቆየ።
- ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ 40 ቀናት አብሮ ቆየ።
- እነዚህን የመሳሰሉ አቆጣጠሮች የመጨረሻውን መልእክት ያዘ ለመምጣት ዋስትና ሆነውለት ተጽፎለታል።

## ጸጋ፣ መሐመድ እና ዐረቦች

## ክፍል ሁለት

«. . . ሌሎች ሕዝቦች የሚሰግዱላቸው አማልክት ጣዖታት ናቸው፣ እግዚአብሔር ግን ሰማይን የፈጠረ አምላክ ነው . . .» (መዝ. 96:5)።

* * *

«. . . የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ . . .» (ዮሐ. 14:15)።

* * *

ሁለቱ ጥቅሶች መሠረታዊ መልእክትን በውስጣቸው እንዳዘሉ ልብ በሉ። መሐመድ ከግል ታሪኩ በመነሣት ሲጠና፣ «እውነትን ፈላጊ» ይመስላል። ብዙዎቹ ዛሬም እውነቱ የቱ ነው ብለው በትጋት እንደሚያጠኑ ሁሉ፣ እርሱም በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተገኝቶ ይህን አድርጓል።

መሐመድ፣ አውቆትም ይሁን ሳያውቅ፣ አቅጣጫ ያሲያዙት የእውቀት ጠቋሚዎች ነበሩት። አንደኛው፣ ከእስልምና ቀድሞ የነበረው የሒንዱ ሃይማኖት ነበር። ሕንዳውያን ከሩቅ ምሥራቅ ተነሥተው የዐረቢያን በረሀ አቋርጠው እስከ አውሮፓ



ይጓጓዟሉ። በዚህ ጉዟቸው ወቅት ሃይማኖታቸውም አብሮ ተንቀሳቀሸ ነው። እምነቱ «ራስን ከዚህ ዓለም በመለየት (በመገንጠል) በሌላኛው ዓለም (በመንፈሳዊው ዓለም) የሚያስገኝ ልምምድ ነው፤» ይህንንም ለረዥም ሰዓታት በመመሰጥ በአማኞቹ ዘንድ ተግባራዊ ይሆናል።

መሐመድ ከመካ ሦስት ማይልስ ከሚርቀው የሒራ ዋሻ ተገኝቶ ያከናውን የነበረው የሒንዱውያንን ሃይማኖታዊ መገለጫን መሠረት በማድረግ እንደ ነበር ይነገራል። ሾልተር አኽማን ከመናፍስት ከሚያገናኘው እምነት ወደ ክርስትና ሲመጣ የሰጠው ምስክርነት፣ «መመሰጥ ክርስቲያናዊ ልምምድ አይደለም፤ እረማውያን ከክፉ መናፍስት ጋር የሚገናኙበት ብቸኛ መንገድ ነው፤ በውጤቱ ባርነትን እንጂ ነጻነትን፣ ሽክምን እንጂ ቅለትን አያመጣም» የሚለው ሰነዱ ከገምት ይገባል።

የሂንዱ እምነት ተከታይ የነበረው ጉሩ ራቢንዳራዝ ማሐራጅ ወደ ክርስትና ከመጣ በኋላ በግል ታሪክ መጽሐፉ ላይ፣ «የዮጋ ልምምዴ በላቀ መመሰጥ ውስጥ ራሴን በማስገኘት ከሂንዱ መለኮታዊ ማንነቶች ጋር ያገናኘኝ ነበር። ይህ ግን ፈጽሞ ከክርስትና ልምምድ የራቀ መሆኑን በጌታ ሆኜ ተረድቼዋለሁ፣» ብሏል።

ጉሩ ገለጣውን የሚያዳብረው 2ኛ ቆሮንቶስ 11:14-15 ላይ ነው፤ «ሰይጣን የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለውጣል። ስለዚህ የሰይጣንም አገልጋዮች የጽድቅ አገልጋዮችን ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ አያስደንቅም፣ በመጨረሻ የሥራቸውን ዋጋ ያገኛሉ...» በማለት የመሐመድ ገለጻና ልምምድ ከምሥራቃውያን የመመሰጥ አምልኮ ተጽዕኖ የታየበት እንደ ነበር ይገመታል። በነቢዩ መሐመድ ሕይወት ውስጥ ሚስቱ ክድጃ፣ አጎቱ እና የኋለኞቹ ሚስቶቹ ድርሻ ነበራቸው። በተለይም ተገለጠልኝ ማለት እንደ ጀመረ አጎቱ ዋራካ ኢብን ናውፋል (Waraqah Ibn Nawfal) ለክድጃ ለሚስቱ ያሳሰባት፣ «ለባለቤትሽ የተገለጠለት የሙሴ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ነው፤ መሐመድ ለዚህ ሕዝብ ነቢይ ሆኖ ተነሥቷልና በአሳቡ እንዲጸና ምከሪው፣» የሚል ነበር።

በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር በሮሜም የምንቀመጥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን . . .» አሉ:: ይህ ገለጻ ዐረቦች ለጸጋ ወንጌል የተጋለጡ ዕድለኞች እንደ ነበሩ ያስረዳል:: በቁጥር 38፤ ጴጥሮስ ንስሐ ስገቡት እና ሊጠመቁ ለተዘጋጁት 3000 ሕዝብ የነገራቸው ተስፋ፣ «. . . የተስፋው ቃል ስእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ እምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና እላቸው . . .» ይህ ገለጻ በዓለም ዙሪያ ተግባራዊ ሆኗል፤ ለዐረቦችም ተመሳሳይ ነው::

ዐረቦች የጸጋን ወንጌል ይሰሙ ዘንድ ስደት ትልቁን ድርሻ ወስዷል፤ የሮም መንግሥት ከ64 ዓ.ም ጀምሮ የፈጸመው አንገልት በርካታ ክርስቲያኖች መጠጊያ ፍለጋ ወደ ዐረቢያ ስላጡ ገስግሰው በዚያ ኖረዋል:: ከዚህም ለዘመናት የወንጌል መልእክት በዐረቦች ዘንድ ሰፍኖ እንደ ነበር ማረጋገጥ ይቻላል::

## እስላምና የሚተገብራቸው መሠረታዊ ደንቦች

መሠረታዊ ደንቦቹ እምስት ሲሆኑ፣ ስድስተኛው ግን ያልተጻፈው ነው፣ መሠየፍ፤

1. ሸሀዳ (Shahada) - «ከአላሕ በቀር አምላክ የለም፣ ነቢዩም መሐመድ ነው::»
2. ሳላት (Salat) - በቀን አምስት ጊዜ ወደ መካ ዞሮ ጸሎት ማቅረብ::
3. ዘካ (Zakat) - ምጽዋት::
4. ሀጂ (Hajj) - ቢያንስ አንድ ጊዜ ወደ መካ ጉዞ ማድረግ::
5. ፆም (Sawm) - በረመዳን ከጠዋት እስከ ማታ መጾም::

ጅሀድ ስድስተኛው በመሆን ይቆጠራል - መሠየፍ ነው:: ይህን ቁርአን 2:256፣ «በሃይማኖት ማስገደድ የለም፣ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፣ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ::»



2:190 «. . . የሚጋደሉዋችሁን (ከሀዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ . . .»

9:29 «. . . መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን አላህና መልክተኛው እርም ያደ ረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሀይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው. . .»

በመጨረሻም፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ እማካኝነት ከሰ ዎች ሁሉ ደረሰ:: ይህም ስመሐመድ እና ስዐረቦች አስቀድሞ ተገልጸ እንደ ነበር ማስተዋል የእግዚአብሔር ታሪክ ሠሪነት በሰዎች ሕይወት ውስጥ እውነት መሆኑን አረጋግጧል::

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

## የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

የኦርቶዶክስ ቃላዊ ፍቺ «ቀጥተኛ ትክክለኛ እምነት» ማለት ነው:: ስለ ምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስንጽፍ ግን፣ «ቅድስት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን» “Holy Orthodox Church” ወይም በብሔራዊ ደረጃ የግሪክ ኦርቶዶክስ፣ የራሺያ ኦርቶዶክስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፣ ወዘተ. . . በሚል ስም እንደሚጠሩ ልብ በማለት ነው::

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እራት ማዕከላትን በዋናነት ይዛለች-ኮንስታንቲኖፕል፣ ኢየሩሳሌም፣ እንጾኪያና እስክንድርያ:: ከእነዚህም ኮንስታንቲኖፕል፣ በተቀሩት ላይ እንጋፋነትና ተሰሚነት ነበራት::

ከእራቱ በተጨማሪ እሥራ አንዱ ቤተ ክርስቲያናት በየመጠሪያ አገሮቻቸው ታውቀዋል፤ የራሺያ፣ የቆጵሮስ፣ የግሪክ፣ የቡልጋሪያ፣ የሩማንያ፣ የሳይቤሪያ፣ የአልባንያ፣ የጆርጂያ፣ የቼኮዝሎቫኪያ፣ የፖላንድና የሲናይ (Sinai) ከአራቱ ጋር በመጠራት አሥራ አምስቱ በዓለም ላይ ታዋቂነትን አግኝተዋል::

ጢሞቴዎስ ዌር (Timothy Ware) በመጽሐፉ፣ «የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ማዕከላዊ አመራር የማትመራ ራስ - ገዝ የሆነች፣ ልዕልናዋን ራሷ በራሷ የምታስጠብቅ ስትሆን፣ አሥራ አምስት ያህሉ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያገናኛቸውና የሚያመሳስላቸው ሁለት ጉዳይ ብቻ ነው፤ የአስተምህሮ (የእምነት) አንድነት አንዱ ሲሆን፣ ሌላኛው የሥርዓተ እምነታቸው (Sacraments) አደራረግ አንድ ዐይነት መሆን ነው» (Ware. ገጽ 15) በማለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አቋም ይገልጻል።

በመሠረቱ፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሦስቱ የክርስትና ዋንኞቹ አንዷ ነች-ከሮማን ካቶሊክ እና ከፕሮቴስታንት። የአማኞች ቁጥራቸው 1 ቢሊዮን ካቶሊክ፣ 500 ሚሊዮን ፕሮቴስታንት፣ 200 ሚሊዮን የኦርቶዶክስ ተከታዮች በዓለም ላይ ይቆጠራሉ።

**የጠራ «ሐዋርያዊ ትውፊት»፡-** ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጠራውን የክርስትና እምነት በመጠበቅ ብቸኛዋ ተጠሪ ነኝ ትላለች። ይህ አባባሏ እውነት ከሆነ፣ ካቶሊኮችንና ፕሮቴስታንቶችን መታገሥ ፈጽሞ አይገባም። በትይዩ ግን፣ ሦስቱም የጠራ እምነት እንዳላቸው ይጽፋሉ፣ ይናገራሉ፣ ያስተምራሉ። ካቶሊኮች ከመስመር የወጡት ኦርቶዶክሶች መሆናቸውንና የሚያስተሳስረውን ገመድ ሆን ብለው በጥሰው በራሳቸው ሌላ የታሪክ ገመድ እንደ ፈበረኩ ዋቢ እየጠሩ ይጽፋሉ። ፕሮቴስታንቶች ደግሞ የተቀሩት ሁለቱ ከጥዋቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት አጥባቢ በመሆን፤ አይገቡ፣ ሲገቡ ያሉትንም የሚመልሱ መሆናቸውን ያብራራሉ፤ ስለ ራሳቸውም ሲናገሩ፣ «በብዙ ተቃውሞ ውስጥ ንጹሑን የክርስትና ታሪክ የጠበቅን ብቸኞች እኛ ነን» ይላሉ።

* * *

ይህን ሁሉ ለመዳኘት የሚቻለው ከአድልዎ ጸድቶ የታሪክ እማኝነትን ዋቢ በመጥራት ነው። ይህ ምስክርነት ይጸና ዘንድ ደጋፊ፣ ተቃዋሚ፣ አማኝ፣ ኢ-አማኒ የጻፉትን ሁሉ አጥልሎ ማየትና የኀሊና ዳኛ በመያዝ መቅረብ ግድ ይሆናል።



የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅርን በከተማ-አቀፍ ደረጃ ታደራጅ እንደ ነበር ይታወቃል፣ የየከተማው ጳጳስ እረኛ ሆኖ በእምነት እና በአስተምህሮ ላይ ጽኑ ጥበቃ ያደርጋል፤ ለዚህም የተመረጡት አምስቱ መንበሮች የተመረጡበት በከተማው የቆዳ ስፋት፣ ወይም በከተማው ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ፣ ወይም በከተማው የፖለቲካ የበላይነት ወይም እምነቱን በተመለከተ ባላቸው ተሰሚነት ነበር።

እነዚህ ጳጳሳት «ፓትሪያርክ» የሚለውን ስም አግኝተው በሮም፣ በኮንስታንቲኖፕል፣ በኢየሩሳሌም፣ በእስክንድርያና በአንጾኪያ ተገኝተዋል።

በ313 ዓ.ም ክርስትና የበርካታ ግዛቶች ሃይማኖት ሆኖ ሕጋዊነትን ሊያገኝ፣ አማንያኑ በግልጽነት፣ በድፍረትና በተግባራዊ እርምጃዎች ወደ ሕዝቡ ለመግባት በቁ። ከ313 በኋላ ቤተ ክርስቲያን-ተኮር የሆኑ የስብሰባ ጉባኤያት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተካሄዱ። እነዚህም በምሥራቁም በምዕራቡም ተደግፈው ያሰፉ ነበሩ። የጉባኤያቱ የስፍራና የጊዜ ስም የኒቂያ በ325፣ የኮንስታንቲኖፕል በ381፣ የኤፌሶን በ431፣ የቀልኬዶን በ451፣ የዳግማይ ኮንስታንቲኖፕል በ553፣ ሣልሣይ ኮንስታንቲኖፕል በ680፣ ዳግማይ ኒቂያ በ787 ተካሂደዋል።

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ሁሉ ፓትሪያርካዊና ዓለም አቀፍ ይዘት ባላቸው ጉባኤያት በተደረጉት ሁሉ ትግሏ ንጹሑን አቋም በመያዝ መዝለቅ ነበር። የሮም ቤተ ክርስቲያን ግን በተቀሩት አራቱ ላይ ለመግነን አቋም መያዟና በየጉባኤው የተካሄዱትን ውሳኔዎች በገዛ ፈቃዷ በማሻሻል የተለየችው እርሷ ነበረች። ኋላም ፕሮቴስታንቶች የሮምን ኦምባ ገነንነት በመቃወም ወጡ፣ እነርሱም የምሥራቅ ኦርቶዶክስን አልወቀሱም። በዚህም መውጣት ከመቃወም ያላለፈ የወጡባቸውን የሚመስሉ የተለያዩ ድርጅቶችን ከፈቱ። ከዚህም የተነሣ፣ «የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ በሐዋርያት መሠረት እና እምነት ጸንታ የቆመች መሆኗ እውነት ሆነ፣» በማለት ስለ ራሷ ትመሰክራለች።

ይህን ምስክርነት ግን ከሚያጉድፍባቸው ቀዳሚው የሮምና የተቀሩት የመለያነታቸው መሠረታዊ ምክንያት «ነገረ መለኮት» አልነበረም፤ ይልቅስ፣ የልዩነት መንሥኤው የባህሳዊ እሴት ጉዳይ፣ የፖለቲካ ኃያልነት፣ የሃይማኖት መገለጫዎችና አደራረጎች ያመጡት ልዩነት ነበር።

የምዕራቡ ዓለም፣ በተለይም በሮም፣ ዋንኛው ቋንቋ ላቲን ነበር፤ በምሥራቁ ዓለም የግሪክ ቋንቋ ተጠሪ ነበር። ሮም በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ከምሥራቆች የትየለሌ የራቀች በመሆኗ፣ በምዕራብ ሮም ለብቻዋ፣ አራቱን ደግሞ በምሥራቅ ለብቻቸው ትቶአቸዋል። ፖለቲካዊ ትግል በሮም እና በኮንስታንቲኖፕል መፈጠሩ ሌላው የመለያ ነጥብ ነበር። መንግሥቱን ማን ይምራው? የሁለቱም ሆኖ የየድርሻቸውን ለማስፈጸም ጥረዋል። ይህን በምሳሌ ለማብራራት ክፍፍሉ ከትንሽ የጀመረ መሆኑን በሚከተሉት እናጢን፦ ምሥራቁና ምዕራቡ የትንሣኤ በዓል መቼ መዋል አለበት? በሚል ጥያቄ ተከራከሩ። ለዚህም ጉዳይ በየዓመቱ ለውይይትና ለውሳኔ ተገኙ። የምዕራቡ ካህናቱ መላጨት የለባቸውም ብለው ሲጠይቁ፣ ምሥራቃውያን ካህናቱ መላጨት አለባቸው በማለት ተወዛገቡ። ምዕራቡ ጻንደ ረብነት (አለማግባት) ተገቢ ነው ሲል፣ የምሥራቁ መጋባትን መከልከል አይገባም አለ። ለጌታ ራት የሚጋገረው እርሾ ይኑርበትን ምሥራቁ ሲፈልግ፣ ያለ እርሾ ይዘጋጅን ምዕራቡ ያስተጋባ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረጸ የሚለው የምሥራቁ ጥያቄ ሲሆን፣ ምዕራቡ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሠርጿል መነጋገሪያው ነበር።

በእነዚህ መነሣሣቶች እያደገ ያለው የልዩነት እርሾ መለያየት ላይ የደረሰው በ1054 ዓ.ም ነበር። ከዚህ በኋላ ምሥራቁ ምዕራቡን፣ ምዕራቡ የምሥራቁን ውጉዝ ከመአርዮስ በማለት ተለያዩ።

ኦርቶዶክስ ከአራቱ ጋር ሆና ከሮም ወጣች ይባል እንጂ፣ ቀደም ሲል በተለይ በ8ኛው ክፍለ ዘመን እስልምና የምሥራቁን የሮምን ግዛት ባጥለቀለቀ ወቅት ተሸናፊ የሆኑት የእስክንድርያ፣



የኢየሩሳሌምና የአንጾኪያ መንበሮች ነበሩ። ለመሸነፋቸው መሠረታዊ ምክንያቱ ደግሞ የኮንስታንቲኖፕል መንበር ጫናን በመፍጠር እና በገገርነት መርኅ ሊያስተዳድራቸው መፈለጉ የእርስ በርስ መናቆርን ፈጥሮ ስለ ነበረ፣ ለእስልምና እንቅስቃሴ ወደፊት መግፋት ዕድሉን አመቻችለት። በተጨማሪም፣ ኦርቶዶክሳውያን ሰባቱ ጉባኤያት በእነርሱ ክልል ተፈጻሚ በመሆናቸው፣ ከሮም ጋር ራሳቸውን እያስተያዩ በሳጭ መሆናቸውን በአደባባይ ተናግረዋል። ዳሩ ግን፣ የየጉባኤያቱ ውሳኔ የመጨረሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የበለጠ አድርገው እንዲገኙ እንደማያደርጋቸው ልብ ማለት ነበረባቸው። ሌላው የምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ የእምነት እሴት ባህላዊ ይዞታን ከመከተል ባሻገር ንጹሑን የሐዋርያት ትምህርት እንደሚሉት በመሠረትነት አላስተናገዱም፤ ለዚህም ሦስት የመነሻ ማረጋገጫን ማንሣት ይችላል።

ሀ. በምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ላይ፣

ለ. በደኅንነት ላይ፣

ሐ. በቅዱሳን መጻሕፍት የበላይነት ላይ እንመካከራለን።

## ሀ. «ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን»

የኦርቶዶክስ አስተምህሮ እና ደኅንነት የተጋመዱ አንድ ነገሮች ናቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በሰባት ምሥጢራት ደርጅታለች፤ ምሥጢረ ጥምቀት (Baptism)፣ መጽሐፈ ቀንዲል (Chrismation/Confirmation)፣ ምሥጢረ ንስሐ (Penance/Confession)፣ ምሥጢረ ቁርባን (Communion)፣ መጽሐፈ ተክሊል (Matrimony)፣ ሜሮን (Unction)፣ መጽሐፈ ክህነት (Holy orders) ይባላሉ። ከእነዚህ ብዙዎች ተለያይተውም ቢሆን ከምዕራቡ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያመሳስሳቸዋል፣ ያቀራርባቸዋል፤ እናም ከልዩነታቸው መጠጋጋታቸው ይበዛል።

የኦርቶዶክሱ ጸሐፊ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያናትን አስመልክቶ ሲናገር፣ «የጢስ አባይ ፏፏቴን መመልከት ተገቢ ነው። ታላቅን ኃይል ቁልቁል በማውረድ ሌት ተቀን ይተጋል፤ ከዚያ እየተግተሰተሰ የሚወርደው ጉልበታም ውኃ ለሌሎች

ጢሞቴዎስ 3:16-17 የተጻፈውን ቃል ከልቤ አመንኩኝ፣ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» የሚለው ቃል የኑሮዩ መልኅቅ ሆኖ ቀዳሚ ሆነልኝ::

ይልቁኑ፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5፣ «አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ»ን ስረዳማ፣ ካህን ሆኜ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሰጠችኝን አደራ እንዴት እንደ ፈጸምኩ በማስተዋል ተሸማቀቅኩ፤ በጉዳዩ ብደነግጥም ግን፣ ከልክ ያለፈ ደስታ በውስጤ ፈሰሰልኝ:: ለካስ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተገኘው አቅም ያለው ኢየሱስ ብቻ ነበር! በካቶሊኮች ዘንድ ግን ካህናት ደካማ ሆነው ሳለ፣ እንደ እኔ ጣልቃ እየገቡ እንዳሉ ቢያስተውሉ እንዴት ደስ ይለኝ!

ብቻ ለብዙዎች ከሕፃንነት እድሜ እስከ ዕውቀት ባለው ጊዜ ሁሉ ለደኅንነትና ለዘላለም ሕይወት ዘማርያምና በቅዱሳን አማላጅነት፣ በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በሚከናወኑት «ምሥጢራት» አማካኝነት ሊገኝ እንደሚችል የታመኑ ሰዎች፣ ይህ ብስራት በእርግጥም ግር ያሰኛቸዋል:: በጸጋ ብቻ ያለ ድካም፣ በክርስቶስ ሥራ ብቻ ጸድቆ መገኘት እንዴት? ያሰኛቸዋል:: ቢያሰኝንም ግን፣ ቅዱስ ቃሉ የገለጠው ብቸኛ እውነት ይኸው ብቻ ነው፤ የተቀረው የሰው ወግ ነው::

የሚገርመው፣ ይህን በድፍረት ለእናንተ መናገር እንኳ የጀመርኩት ማስተዋሌ እየጨመረ ባለበት ስድስተኛው ዓመት ላይ መሆኑን ተገንዝቡልኝ:: በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በደሜ ውስጥ እንደ ተዋሀደ ያህል የሆነብኝ ካቶሊክነት በአንድ ወገን ቆሞ፣ «ብቸኛው ተደማጭና ልዕልና ያላት ባለሥልጣን እርሷው እንደ ሆነች» ሲያሳስበኝ፤ በሌላ ወገን፣ «ለእምነትና ለተግባሬ ብቸኛው ባለሥልጣን ቃሉ ብቻ እንደ ሆነ አምን ነበር::» እነዚህ ሁለቱ



እየተገዳደሩኝ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አቆይተውኝ ነበር:: ትግሉ ግን ለሁለት ጌቶች መገዛት ማንም እንደማይችል በማስተዋል ለቃሉ መገዛትን አስመርጦኝ አሸነፍኩ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሮማ ካቶሊክ ከ«እኔ በላይ» ባይነት ከውድድሩ ውጭ ሆነ::

በ1985 (እ.ኤ.አ.) ጸጋ አሸነፈ:: የሮም ካቶሊክን የዋስትና ምሽግ ትቼ ጥሼ ወጣሁ:: አጣጣሌ ቀላል አልነበረም፤ መከራ በውስጡ አለበት፣ የኅሊና ሙግት አብሮት አለ:: ቢሆንም፣ ለእውነት ማደርን የመሰለ ምንም የለም:: ከልቤ ንስሐ ገባሁ:: በእግዚአብሔር መካከል ልገኝ ባልኩበት በደል አለቀስኩኝ:: በሁኔታዎች ላይ ያልተመቻቸው የእግዚአብሔር ምርጫ ለእኔ ዋስትና ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ በምስጋና እየሞላኝ በጌታ ፊት ቀረብኩኝ:: ኢሳይያስ 53:5 ጽኑ ትርጉሙን ሰጠኝ፣ «ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፣ ስለ በደላችን ደቀቀ፣ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተ ፈወስን»፣ ለእኔም ፈውስ ሰጠኝ::

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ከለቀቅኩኝ በኋላ፣ እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ ከጐኔ ቆሞ አየሁኝ (እ.ኤ.አ.) በ1991 ዓ.ም ወደ እስያ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆኜ በወንጌላዊነት ወጣሁ::

አንባቢዬ ሆይ፣ ሃይማኖታዊ ተግባራትንና ወጎችን በማከናወን ላይ ብቻ ተደግፈህ ከሆነ፣ አስብበት:: ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሠራው የተጠናቀቀ ሥራ ውጭ ምንም መደገፊያ የለም:: የእግዚአብሔር ቃል በ1ኛ ጴጥሮስ 1:18-19፣ «ከአባቶቻችሁ በወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ . . .» መባሉን ልብ እንበል:: ደሙ ነው ኃጢአታችንን የሚሸፍን፣ የመዋጀታችንና የመዳናችን ምሥጢር ክርስቶስ ነው:: እርሱ በሠራው ሥራ ላይ እንከን ማውጣት አይቻልም፤ የሁሉ ነገር መደምደሚያ ነውና:: 1ኛ ጴጥሮስ 2:24፣ «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ

ራሱ በሥጋው ኃጢአታችሁን በእንጨት ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስልም ተፈወሳችሁ» ይላችኋል።

ይህን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወታችሁ ጋብዙት፤ እርሱ አስደናቂ ተአምሩን ያደርጋል፤ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነውና» (ዮሐንስ 3፡6)።

## እያንዳንዱ ካቶሊክ ሊያውቀው የተገባ መልእክት

እያንዳንዱ ካቶሊክ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይፈልጋል፤ ይህንንም በኑሮው ሁሉ በመግለጽ ይመሰክራል፤ በውጤቱም ከዚህ ምድራዊ ሕይወት ባሻገር ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚኖር እርግጠኛ ነው።

አንድ ካቶሊክ ይህን አምኖ መኖር፣ ዕቅዱንና ግቡን አመላካች ስለሆነ፣ የተመሰገነ ራእይ ነው። ይህ የኑሮ ስልት ግን በድምዳሚው ከእግዚአብሔር መንፈስ ሳይሆን፣ ላልታሰበው ለተቃራኒው ቢዳርግ ምን ይሰማዋል?

እኔ፣ ሪቻርድ ፒተር ቤኔት፣ ለ22 ዓመታት በዶሚኒካን ካህን ሆኜ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አገለግል ነበር። ኋላ ግን፣ ሁሉን ጥዬ ወጣሁ። የሸሸሁበት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉኝ። ያንን ደግሞ በጋራ ማስረዳት የምችለው ለተከታዮቹ ጥያቄዎች መልስ እየሰጠን በመሄድ ስንዘልቅ ነው። እናም ካቶሊክ ከሆናችሁ፣ ትዕግሥትን እንደ ገንዘብ በመሸመት በአንድ ቁጭታ አብረን እንናበብ።

### *ጥያቄ 1፣ የማን ቃል እውነተኛ ይሁን?*

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ «የጳጳሱ ቃል ብቻ እውነተኛ ነው» ትላለች። «. . . ከእርሳቸው ቢሮ የሚሰማውና የሚወጣው ቀኖና ሁሉ ሊሻር የማይችል፣ የሚጸና እውነተኛ መመሪያና ቃል ነው» ይላል Canon 479።

### *መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፡-*

«የእግዚአብሔር ቃል ብቻ እውነተኛ ነው» ይላል። ኢየሱስ ወደ አባቱ በጸለየ ጊዜ፣ «በእውነትህ ቀድሳቸው፣ ቃልህ እውነት ነው» አለ (ዮሐ. 17፡17)። በማቴዎስ 4፡4 ደግሞ፣ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ



አይኖርም» በማለት አስተማረ። ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞ. 3፡16 ደግሞ መሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አስተማረ፣ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ . . .» በማለት አሳወቀ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ እውነተኛ እና ባለሥልጣን መሆኑን በማስጠንቀቅም አስተማረ፣ «. . . ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፣ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ» በማለት፣ በእነርሱ ዘንድ ያለው ሁሉ ከወግ እና ከሰው ሥርዓት ጋር ተያያዥ መሆኑን አሳወቃቸው።

### *ጥያቄ 2፣ ምስሎችን እንጠቀም ዘንድ ይገባልን?*

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ «አዎን፣ በሚገባ እንጠቀማለን» የሚል ምላሽ ትሰጣለች።

«የተቀደሱ ምስሎች በቤተ ክርስቲያን መገኘታቸው እምነትን ጉልበታም በማድረግ እና ኃይልን በውስጣችን በመፍጠር ያግዛሉ . . .» (Canon 1188) ይላል።

### *መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣*

ፈጽሞ ምስልን እንጠቀም ዘንድ አይገባም ይላል። ይህንንም ዘጸአት 20፡4-5፣ «በላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ ከምድርም በውኃ ካለው ውስጥ ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም . . .» ይላል። የሮማ ቤተ ክርስቲያን ግን ምስሎችን (ቅርጾችን) መጠቀም ብቻ ሳይሆን፣ ለእነርሱ ተገቢ ስግደትና አክብሮት መስጠት ይገባል ባይ ነች፤ ዋንኛው ጳጳስም ይህን መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

### *ጥያቄ 3፣ ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው በየጊዜው ነውን?*

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ «አዎን፣ በየጊዜው ነው» የሚል ምላሽ አላት። «የመዋጀት ሥራ በየጊዜው በሚከናወን ሥርዓተ ቁርባን አማካኝነት በተደጋጋሚ ክርስቶስ መሥዋዕት ይሆናል፤

ይህንንም ካህናቱ በየጊዜው ተፈጻሚ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው» (Canon 904) ይላል።

### መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሚለው . . .

«ኢየሱስ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ብቻ ነው፤ አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብሩ ዙፋን አለ» ይላል። ይህንንም፣ «. . . ኢየሱስ ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ፣ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ» (ዮሐ. 19:30) በማለት ያረጋግጣል።

የካቶሊክ ካህናት በየቀኑ እየቆሙ ለመሥዋዕት የተገባውን ዝግጅት ይክውናሉ። ይህ ሥራ ግን የማንንም ኃጢአት ፈቶ አያደርግም፣ ምሕረትንም አያሰጥም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟአል፤ እርሱ ግን (ኢየሱስ ክርስቶስ) ስለ ኃጢአት አንዴ መሥዋዕትን ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ» (ዕብ. 10:11፣12) በማለት ያበስራል።

### ጥያቄ 4፣ ካህን አስፈላጊ ነውን?

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ «ካህናት ያስፈልጋሉ» ትላለች።

«ካህናት የክርስቶስን የክህነት አገልግሎት የሚካፈሉ አገልጋዮች ናቸው . . . ሕዝቡን ወደ ቅዱስና አክብሮት ወደ ሞላው አምልኮ ያመቻቻሉ . . .» (Canon 835) ይላል።

### መጽሐፍ ቅዱስ ግን...

አማኞች ሁሉ ካህናት መሆናቸውን በመግለጽ፣ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔርን በየግላቸው የማመስገንና የማምለክ አቅም እንዳላቸው ያረጋግጣል። 1ኛ ጴጥሮስ 2:9፣ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁ የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት . . . ናችሁ» በማለት፣ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ጸጋው ዙፋን ፊት መቅረብ መቻሉን እያረጋገጠ፣ ብቸኛ ሊቀ ካህናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያበስራል። ይህ ደግሞ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5፣6 ላይ፣



«አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ ነው እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» በማለት ጽኑ ምላሽ ይሰጣል።

### ጥያቄ 5፣ ጥምቀት ያድናል?

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ «ድኅነት (መዳን) የሚጀምረው በጥምቀት ነው» ትላለች። «መጠመቅ ወደ ሌሎች የእግዚአብሔር ምሥጢራት የመግቢያ ቁልፍ ነው። ወንዶችና ሴቶች ሁሉ በተጠመቁ ወቅት ከኃጢአታቸው ይታጠባሉ፣ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆንም ዳግም ይወለዳሉ፣ ከክርስቶስም ጋር ይኖራሉ . . . » (Canon 849) ይላል።

### መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣

የሰው የትኛውም በጎ ሥራ ለእግዚአብሔር መንግሥት አያበቃም፣ በክርስቶስ ላይ ያለ እምነት ብቻ ሰዎችን ያድናል ይላል። የእርሱ የሆኑት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ጥል ወደ ሰላምና እርቅ የለወጠው የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሥራ ነው፤ ያንን ማመን ጸጋ ነው። ኤፌሶን 2:8፣9 እንዲህ ይላል፣ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» ዮሐንስ 6:29 ደግሞ፣ «ኢየሱስ መልሶ . . . ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።» ሮሜ 11:6፣ «በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል» በማለት፣ ጥምቀት ምንም ድርሻ እንደሌለው ያበስራል።

### እንኪያስ እንዴት መዳን ይቻላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአተኛ መሆናችንን እናስተውል ዘንድ ይጠይቃል። ኢሳይያስ 64:4-5፣ እኛ ግን . . . ሳናቋርጥ ኀጢአት በመሥራታችን እነሆ ተቆጣህ፣ ታዲያ እንዴት መዳን እንችላለን? ይላል። ኤርምያስ 17:9፣ «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?» በማለት እቅጩን ይናገራል።

ይህን በመፈጸም ታዋቂ የሆነችው የግብጽ ንግሥት ሃትሻፕሱት (1490-1468 ዓ.ዓ.) በምታደርገው ግብይት ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንደ ነበራት በዜና መዋዕሏ ተጽፏል:: ከዚህች ንግሥት በኋላ የተነሡ ፈርዖኖች ተመሳሳይ ንግድ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጋር እንደ ነበራቸው ኢጣሊያዊ ሊቅ ኮንቲ ሮሲኒ ጽፎበታል::

በግብጽ ቴሰብ በተባለች ከተማ በሚገኘው የመቅደስ ሥዕል ላይ ፑንት ምድር የነበሩትን የመርከብ ዓይነቶች ከነሸቀጣቸው ያሳያል:: ይህም ግንኙነት እንደ ነበረ ያመለክታል::

በተቀራራቢ ዘመንም ከተከናወኑ ገለጻዎች ውስጥ 1ኛ ነገሥት 10 ዋናው ነው:: ንጉሥ ሰለሞን (974-932 ዓ.ዓ) በሥልጣኑ ላይ የነበረ የእስራኤል ንጉሥ ነው:: ይህ ንጉሥ በቀይ ባሕር ሰሜናዊ ጫፍ ላይ ወደብ አሠርቷል፤ ከዚያም መርከቦችን በመላክ «ኦፊር» ከተባለ ስፍራ ወርቅና ጥድ ያጓጉዝ ነበር::

የኦፊር ትክክለኛ ቦታ የት እንደ ሆነ በውል ባይታወቅም፣ ቀይ ባሕርን የሚያዋስን የአፍሪካ ጠረፍ ሳይሆን አይቀርም:: አንዳንድ ተመራማሪዎች ኦፊር «ደንከል»ን ይመለከታል ይላሉ:: በዚያ ደግሞ «አፋር» ተብሎ የሚጠራ ሕዝብ በመኖሩ፣ ከእነርሱ ጋር ሊገናኝ ይችላል:: 1ኛ ነገሥት 10:11 (ከኦፊር ወርቅ ያመጡለት የኪራም መርከቦች ከዚያው ከኦፊር ብዙ የጥድ እንጨትና የከበረ ዕንቁ አምጥተውለት ነበር) ይላል:: 1ኛ ነገሥት 10 የንግሥት ሳባ ጉብኝትን የሚመለከት ነው::

ሳባ፡- በዕንቆቅልሽ ልትፈትነው ሄደች::

- ብዙ የክብር አጃቢዎችን አስከትላለች::
- በግመሎች የተጫነ ሽቶ፣ የከበረ ዕንቁና ብዙ ወርቅ አስይዛለች::
- ሄዳም ለሰሎሞን ያቀረበችውን ጥያቄ ሰሎሞን መስሰሳት- ተረጎመላት::
- የሠራውን ቤተ መንግሥት አየች፣ ገበታውን አደነቀች::



- ንግሥቲቱ የቤተ መንግሥቱን ሠራተኞች የሥራ አደረጃጀትና የደንብ ልብስ አየች::
- በቤተ መቅደስ የሚያቀርባቸውን መሥዋዕቶችን ሁሉ ተመለከተች::
- ይህ ሁሉ ከሰማችው በልጦ አገኘችው::

1ኛ ነገሥት 10:13፣ «ንጉሥ ሰሎሞን ከተለመደው የልግሥና ስጦታው ጋር የሳባ ንግሥት የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት:: ከዚህ በኋላ ንግሥት ሳባ ከክብር አጃቢዎችዋ ጋር ወደ አገርዋ ተመልሳ ሄደች» በማለት ይጨርሳል:: 1ኛ ነገሥት 10 ከገለጸው ውጭ ግን በ14ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተጽፎ የነበረው «ክብረ ነገሥት» የአበሻን መንግሥት በሥልጣን ለዘንተ ዓለም ለማኖር የተፈበረከ አፈ ታሪክን ይዞ ወጥቷል:: ታሪኩ «ንግሥት ሳባ፡- ማክዳ በመባል በትግራይ ላይ መንገሷን፣ በሀብት የበለጸገች በመሆኗ ከሕንድ እስከ አስዋን ትነግድ እንደ ነበረ፣ በተደያኸርም ማክዳ ከሰሎሞን አርግዛ እንደ ተመለሰች፣ የወለደችው ልጅ የዳዊት ስርወ መንግሥት በመሆን ስሙ ቀዳማዊ ምኒልክ በመባል የሰሎሞናዊ ነገሥታቱ የዘር ሐረግ እንደ መሠረተ ይናገራል::» ይህ ግን በአፈ ታሪክ የሚመደብ ነው::

«ክብረ ነገሥቱ» ምኒልክ ሲያድግ አባቱን ንጉሥ ሰሎሞንን ኢየሩሳሌም ሄዶ ጐብኝቶ ብዙ የእስራኤላውያን የበኩር ልጆችን አስከትሎ መመለሱ፣ እነርሱም እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝበ እስራኤል ሰጥቶ የነበረውን ታቦት አዛሪያ በተባለው የሳዶቅ በኩር ልጅ ሰርቆ በድብቅ ይዘው እንዳመጡ ይተርካል:: በጎንደር ይኖሩ የነበሩ ፈላሻዎች የእነርሱ ዘር የሆኑ ቤተ-እስራኤሎች ናቸው ተብሎ ሲታመን፣ ቀሳውስቱ ደግሞ የሊቀ ካህኑ የሳዶቅ ዘሮች ተደርገው ቀርበዋል:: ከዚያን ጊዜ ወዲህ የነገሡ ነገሥታትም «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» ብለው ራሳቸውን ለመጥራታቸው ይኸው ትውፊት መነሻ ሆኗል::

ጃንስና ኤልሳቤጥ ሞንሮም ባስፈሩት ሐተታ ይህ አፈ ታሪክ በ11ኛው ክፍለ ዘመን እኩሌታ ላይ አበሾች የፈጠሩት ትረካ ነው

በማለት መለኮታዊ መብትን በመተረት ለመግዛት ያመቻቸ መንሥኤ ነው ብለው ጽፈዋል::

**የፋርስ መንግሥትን በተመለከተ**፡- የፋርስ መንግሥት የገነነበት ወቅት ታላቁ ዳርዮስ (525-485 ዓ.ዓ) በሥልጣን የገዛበት ዘመን ዋንኛው ተጠሪ ነው:: በዚህ ወቅት ዳርዮስ ከግብጽ ጋር ግንኙነት ነበረው:: ይህ ግንኙነት የፋርስን ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች ቀይ ባሕር አካባቢ ወዳሉት አገሮች እና ወደ ኢትዮጵያም ሰርጎ የመግባት ዕድል ሳያስገኝ አልቀረም::

ይህን መንግሥት በተመለከተ በዳንኤል 5:30፣ «በዚያን ሌሊት የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር ተገደለ . . . ዳርዮስም መንግሥቱን ወረሰ::» ዳንኤል 6:1፣ «ዳርዮስም በመንግሥቱ ግዛት ሁሉ ላይ እንዲያስተዳድሩ መቶ ሀያ መሳፍንት ለመሾም ፈለገ . . .» ዳንኤል 6:28፣ «ዳንኤልም በዳርዮስና በፋርሱ ንጉሥ በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ሁሉ እንደ ተከበረ ኖረ . . .» ይላል:: ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍንጭ ነው::

ከዚህ በኋላ በግብጽ አካባቢ ካሉ አገራት ጋር ግንኙነት የፈጠረው የታላቁ እስክንድር (356-323 ዓ.ዓ) እንቅስቃሴ ነው:: ግሪኮች የቀይ ባሕር አካባቢ አገሮችን በዘመናቸው ደርሰው ነበር:: የግሪክ ነጋዴዎች በየአገራቱ ባህላቸውን እያስፋፉ ባለቡት ዘመን ተከትለዋቸው የመጡት ሮማውያን በቀይ ባሕር ዙሪያ ትኩረት በማድረግ ባህላዊ አስተሳሰባቸውን የማስፈን እንቅስቃሴ አድርገዋል:: ሮማውያን የንግድ የአቅጣጫ ካርታን ባዘጋጁበት መረብ ላይ የአክሱም መንግሥትን አመልክተው አዶሊስ ዋና ወደብዋ እንደ ነበረች በጊዜው ዘሶካረስ የተባለ ንጉሥዋ የግሪክ ቋንቋ ዕውቀት እንደ ነበረው ጽፈዋል::

እንግዲህ ይህ የጥንታዊ ኢትዮጵያ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ አውሮፓ፣ እስያና አፍሪካ የተገናኙበት ክልል እንደ ነበረ መገንዘብ ይቻላል:: እንግዲህ አገሪቱ የግሪክንና የሮማን የሜድትራንያን ባህል፣ በተያያዥም የሕንድና የፋርስ የዓረባዊ ባህል ሥልጣኔ ያቆጠቆጠባቸው ስፍራዎች ነበሩ:: ይህን ለማረጋገጥ፣ የግሪክ አማልክት በቅድመ-ክርስትና ታሪክ ላይ



ታይተዋል:: በአክሱም የሐውልት ላይ ጽሑፎች ዙየስ፣ ፖሲዲያን እና አሬስ የተባለ የግሪኮች አማልክት ስም አዶሊስ በተገኘው ጥንታዊ ሐውልት ላይ መኖሩ ተረጋግጧል:: የምሥራቁን ዓለም በተመለከተ፡- በምሥራቅና በአፍሪካ የተለመደ የዘንዶ አምልኮ ተንሰራፍቶ እንደ ነበር የሚያመለክት ሐውልት አክሱም ተገኝቷል- በዚያም ላይ የእባብ ምስል ተቀርጾ ይታያል::

**ፋርስን በተመለከተ**፡- እነርሱ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ በሚቆጥሩት «ኢቬስታ» በተባለው መጽሐፍ ላይ ዘንዶን የማምለክ ሥርዓት በኢትዮጵያ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ እንደ ነበር ተገልጿል::

**ደቡብ ዐረቢያን በተመለከተ**፡- ሳባዊ አምልኮዎች በኢትዮጵያ ታይተዋል:: ይህም የሚታወቀው የጣዖት አምልኮዎች በስፋት ተሰራጭተው እንደ ነበር በንጉሥ ዔዛና ገድሎች ላይ ተረጋግጧል:: እርሱ የክርስትናን እምነት ከመቀበሉ በፊት በግዕዝ ፊደል ባስቀረጻቸው ሐውልቶች ላይ የአረማውያንን አማልክት ስሞች አስቀርጾአል::

በትግራይ መንደሮች (ሃና ሃወልቲ ሜሎዛ) አልሞካ ለተባለ የሰማይ አምላክ የተሠራ ቤተ መቅደስ ተገኝቷል:: በአክሱም አካባቢ ያሉ መሠዊያዎቹ «ሲን» የተባለ የሳባውያን የጨረቃ አምላክ ምልክት ተስሎባቸው ይገኛሉ:: ይህም ከዚህ አምላክ የተያያዘ መሆኑን ያመለክታል:: ኢዛና ቤጃዎችን አሸንፎ ከምርኮ ሲመለስ ድል ስለ ሰጠው ለአሬስ ክብር ሐውልት አሠርቷል:: በዙሪያ ገቡ ያሉ አገራት በጥንት አካባቢ ከፍተኛ ለውጥ አምጥተዋል፤ በተለይም ኩሻውያን ሰፍረውበት ነበር የተባለው የጥንት /የኢትዮጵያ/ ክልል በሴማውያን መፍለስ እና መቀየጥ አገራዊ የሆነውን ባህላዊ እምነት ፈጥሯል::

ከኩሻዊ ሕዝቦች ዋንኞቹ ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች ናቸው:: እነርሱ የፍጥረታት ፈጣሪ እንዳለ በማመን «ዋቃ» በማለት ይጠሩታል:: መለኮታዊ ኃይላትና መናፍስት መኖርን የዋቃ ማንነት የሚገለጥባቸው «አያና፣ ባር፣ ውቃቢ . . .» በመባል ይጠሩ ነበር:: «ዛር» ከአገው የተገኘ ስያሜ ሲሆን፣ አገዎች

